ሳምንታዊ የቢዝነስ መረጃዎች

በኢንፎሜሽንና ኮ/ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት

ከየካቲት 24- 30/ 2018 ዓ.ም

MARCH 3-9/2026

1. የአፍሪካ ነፃ የንግድ ቀጣና የኢትዮጵያን የንግድ ምህዳር ወደ ላቀ ምዕራፍ የሚያሸጋግር ታላቅ ዕድል ነው

ኢዜአ፡ የካቲት 27/2018

የአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጣና (AfCFTA) የኢትዮጵያን የንግድ ምህዳር ወደ ላቀ ምዕራፍ የሚያሸጋግር ታላቅ ዕድል ከመሆኑም ባለፈ ከጎረቤት አገራት ጋር ያለውን የንግድ ትስስር ወደ ላቀ ደረጃ እንደሚያሸጋግር የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት አስታወቀ።

የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ዋና ጸሀፊ ቀነኒሳ ለሚ (ዶ/ር) ከኢዜአ ጋር ባደረጉት ቆይታ፤ የአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጠና መመስረት ለኢትዮጵያ ነጋዴዎች ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎችን ያስገኛል ብለዋል፡፡

በዚህም ነጋዴዎች ምርታቸውን በሀገር ውስጥ ብቻ ሳይሆን በመላው አፍሪካ ያለ ታሪፍና የንግድ መሰናክል የመሸጥ ዕድል እንደሚያገኙ ተናግረዋል፡፡

በህጋዊ ውድድር ውስጥ ማለፋቸው ነጋዴዎች ራሳቸውን ዘወትር እንዲያሻሽሉ ያደርጋል ያሉት ዋና ጸሐፊው አዳዲስ አሰራሮችን እንዲከተሉና ይበልጥ ውጤታማ እንዲሆኑ ምቹ ዕድል እንደሚፈጠርም ገልጸዋል፡፡

የገበያው መከፈት ከሌሎች አፍሪካውያን ነጋዴዎች ጋር የንግድ ስልቶችን ለመቅሰም ትልቅ አጋጣሚ እንደሚፈጥር ተናግረዋል፡፡

የሀገሪቱ የንግድ ህጎች ከአህጉራዊው ስርዓት ጋር መጣጣማቸው የውጭ ኢንቨስተሮችን ይስባል፤ ይህም ለዜጎች የስራ ዕድል በመፍጠር ለሀገራዊ ብልጽግና መሰረት ይሆናል።

ኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት በዕቃ ንግድ ፕሮቶኮል ላይ ትኩረት አድርጋ እየሰራች መሆኑን ጠቅሰው፤ ከደቡብ አፍሪካ፣ ከኬኒያና ከሶማሊያ ጋር የንግድ ልውውጥ መጀመሩንም ገልጸዋል፡፡

ምክር ቤቱ ነጋዴዎች ያላቸውን ጸጋ ለይተው እንዲያውቁና በምርቶቻቸው ላይ እሴት በመጨመር በዓለም አቀፍ ገበያ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ አስፈላጊውን ስልጠናና ድጋፍ እያደረገ እንደሚገኝም ገልጸዋል፡፡

https://www.ena.et/web/amh/w/amh_8437218

2. የቡና አምራቾችና አቅራቢዎች በእጃቸው ያለውን የቡና ምርት በፍጥነት ወደ ገበያ ሊያቀርቡ ይገባል

ኢዜአ፡ የካቲት 26/2018

የቡና አምራቾችና አቅራቢዎች በእጃቸው ያለውን የቡና ምርት በፍጥነት ወደ ገበያ ሊያቀርቡ እንደሚገባ የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን አሳሰበ።

ባለፉት ሁለት ወራት የቡና ዋጋ በዓለም አቀፍ ደረጃ እየቀነሰ መምጣቱንም ዋና ዳይሬክተሩ አዱኛ ደበላ(ዶ/ር) ገልፀዋል።

የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ዋና ዳይሬክተር አዱኛ ደበላ(ዶ/ር) እንዳሉት፣ ባለፉት አምስት ዓመታት በመጠንና በጥራት የተሻለ ቡና ለዓለም ገበያ በማቅረብ የተሻለ ገቢ ማግኘት ተችሏል።

የቡና እሴት ሰንሰለትን ማሳጠርና ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ የሚያስችሉ ተግባራት መከናወናቸውን ጠቁመው፤ በዘንድሮ በጀት ዓመት 1 ነጥብ 5 ሚሊየን ሜትሪክ ቶን ቡና መመረቱን ተናግረዋል።

በ2017 በጀት ዓመት 2 ነጥብ 6 ቢሊየን ዶላር በላይ ከቡና ወጪ ንግድ ገቢ መገኘቱን ገልፀው፣ በዘንድሮ በጀት ዓመትም 3 ቢሊየን ዶላር ገቢ ለማግኘት ታቅዶ እየተሰራ ይገኛል ብለዋል።

ባለፉት ሁለት ወራት የቡና ዋጋ በዓለም አቀፍ ገበያ እየቀነሰ መምጣቱን አንስተው፤ የጥራት ደረጃን በማሻሻል፣ ስፔሻሊቲ ቡናን በማቅረብና ተወዳዳሪነትን በማሳደግ የታቀደውን ለማሳካት እንደሚሰራም አስታውቀዋል።

https://www.ena.et/web/amh/w/amh_8427518

3. የኢትዮጵያ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ "ንዋይ" የተሰኘ የሞባይል መተግበሪያ ይፋ አደረገ

ኤፍ.ኤም.ሲ፡ የካቲት 26፣ 2018

የኢትዮጵያ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ የካፒታል ገበያን ለሁሉም ዜጎች ተደራሽ ለማድረግ የሚያስችል "ንዋይ" የተሰኘ የሞባይል ግብይት መተግበሪያ በዛሬው ዕለት ይፋ አድርጓል። መተግበሪያው በሀገሪቱ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ማንኛውም ግለሰብ ሞባይል ስልኩን በመጠቀም በአክሲዮን እና በዕዳ ሰነዶች ግብይት ላይ በቀጥታ እንዲሳተፍ እድል የሚሰጥ ነው።

የኢትዮጵያ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ዋና ስራ አስፈፃሚ ጥላሁን እስማኤል (ዶ/ር) በመተግበሪያው የምረቃ ሥነ ሥርዓት ላይ እንዳሉት÷ "ንዋይ" ገበያውን በእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ እጅ ላይ ተደራሽ ያደርገዋል። መተግበሪያው ባለሀብቶች በማንኛውም ጊዜና ቦታ ሆነው በሀገሪቱ የኢኮኖሚ እድገት ውስጥ በቀጥታ እንዲሳተፉ የሚያስችል መሆኑን ጠቅሰው÷ የሰነድ ግዢና ሽያጭ ትዕዛዞችን በስልክ ማስተላለፍና መፈጸም እንደሚያስችል ተናግረዋል። የኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር ሀና ተልኸቁ በበኩላቸው÷ በርካታ ሀገራት ወደዚህ ዓይነት የቴክኖሎጂ ሥርዓት ለመድረስ ረጅም ጊዜ እንደወሰደባቸው አስታውሰዋል።

ኢትዮጵያ ግን ከሌሎች ሀገራት ተሞክሮ በመማር በአጭር ጊዜ ውስጥ ዘመናዊ የገበያ ሥርዓት መገንባቷን አስረድተዋል።በሁሉም የሀገሪቱ ጫፍ ያሉ ዜጎች የኢንቨስትመንት አካውንት በመክፈት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማንዛቤ መፍጠር እንደሚገባ ተናግረዋል።

https://www.fanamc.com/archives/310780

4. 4ኛው የኢትዮጵያ የኢንቨስትመንት ፎረም መጋቢት 17 እና 18 ይካሄዳል

ኤፍ.ኤም.ሲ፡ የካቲት 24፣ 2018

4ኛው የኢትዮጵያ የኢንቨስትመንት ፎረም የፊታችን መጋቢት 17 እና 18 በአዲስ አበባ ይካሄዳል ። የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽነር ዘለቀ ተመስገን (ዶ/ር) በሰጡት መግለጫ፤ ፎረሙ ኢትዮጵያ ያላትን ምቹ የኢንቨስትመንት ምህዳር በስፋት የሚያሳይና የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው የፈጠረውን ምቹ የኢንቨስትመንት እድል ለማስተዋወቅ የሚያግዝ ነው ብለዋል፡፡

"ኢትዮጵያ ለኢንቨስትመንት ዝግጁ ናት" በሚል መሪ ሃሳብ ለሁለት ቀናት በሚካሄደው ፎረም ላይ ከ800 በላይ ዓለም አቀፍ ባለሀብቶች፣ የንግድ መሪዎች፣ ፖሊሲ አውጪዎች እንዲሁም የልማት አጋሮች እንደሚሳተፉ ጠቁመዋል፡፡በ3ኛው የኢንቨስትመንት ፎረም ከ1 ነጥብ 6 ቢሊየን ዶላር በላይ ስምምነቶች መደረጋቸውን አስታውሰው፤ በዘንድሮ ዓመት ከትላልቅ ድርጅቶች ጋር ከ2 ነጥብ 4 ቢሊየን ዶላር በላይ ስምምነቶች ለማድረግ ታቅዷል ነው ያሉት፡፡ ፎረሙን የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ከገንዘብ ሚኒስቴርና ከልማት አጋር ድርጅቶች ጋር በመተባበር እንደሚያዘጋጀው ተገልጿል።

https://www.fanamc.com/archives/310651

5. Ethiopia Inks Bilateral Market Access Protocol with Japan at WTO Headquarters

ENA: March 5, 2026

Ethiopia and Japan have signed a Bilateral Market Access Protocol at the headquarters of the World Trade Organization (WTO) in Geneva, marking another important milestone in Ethiopia's ongoing accession process to the global trade body.

The agreement was concluded by Tsegab Kebebew Daka, Permanent Representative of Ethiopia to the UN Office at Geneva and other International Organizations in Switzerland and Nagai Katsuro, Permanent Representative of Japan to the WTO.

With this latest agreement, Ethiopia has now concluded bilateral market access negotiations with seven WTO members including China, Turkey, Argentina, Russia, Brazil, Thailand, and Japan.

With this latest agreement, Ethiopia has now concluded bilateral market access negotiations with seven WTO members including China, Turkey, Argentina, Russia, Brazil, Thailand, and Japan.

https://www.ena.et/web/eng/w/eng_842827

6. Ethiopia Secures over 288 million USD from Horticulture Exports in Seven Months: Ministry

ENA: February 27, 2026

Ethiopia has generated 288.48 million dollars from horticulture exports during the first seven months of the current Ethiopian fiscal year, according to Ministry of Agriculture.

Agriculture Minister Addisu Arega said the country earned 288.48 million dollars from the export of 160,317.79 tons of horticultural products, including flowers, fruits and vegetables. The performance represents 70.9 percent of the planned export target for the reporting period.

He noted that horticulture, alongside coffee, remains one of Ethiopia's priority export commodities, emphasizing its strategic contribution to foreign exchange earnings.

https://www.ena.et/web/eng/w/eng_8396911

7.Bishoftu Airport Project Requires Massive Workforce Supply

The Reporter: March 7, 2026

Construction of the Bishoftu International Airport is projected to require a workforce supply that could annually rise and reach 100,000 workers by 2029, according to a Labor Management Procedure document.

Launched by Ethiopian Airlines Group (EAG) recently, the project is intended to relieve congestion at Bole International Airport and support the airline Group's long term expansion as a global aviation hub.

According to the document, labor demand will increase rapidly during the construction phase, with workforce demand projections climbing from 50,000 workers in 2026 and 70,000 in 2027. The project will require 90,000 workforce in 2028, and eventually reaching 100,000 by 2029 as construction activities intensify.

The project documents note that while some highly specialized engineers and supervisors may be recruited from outside the immediate project area, priority will be given to local recruitment for semi-skilled and unskilled labor positions in order to limit labor migration pressures.

In parallel with labor planning, the African Development Bank (AfDB) has issued a Request for Expressions of Interest (EOI) seeking consulting firm to serve as the Lenders' Environmental and Social Advisor (LESA), to undertake an independent assessment of the environmental and social aspects of BIA for the benefit of the Lenders prior to decision making. Ethiopian Airlines designated AfDB as Initial Mandated Lead Arranger (IMLA).

https://www.thereporterethiopia.com/49594/

8. Ethio Telecom And Ericsson Sign Network Expansion And Modernization Agreement At MWC Barcelona

FMC: March 5, 2026

Ethio telecom and Ericsson have signed a network expansion and modernization agreement aimed at strengthening Ethiopia's digital infrastructure, the company announced.

The agreement was concluded at the Mobile World Congress in Barcelona and represents another milestone in the implementation of Ethio telecom's three-year Next Horizon Strategy, which targets modernization and expansion of national connectivity.

The project encompasses network expansion, upgrades, 4G layering, and deployment of new capabilities across 1,500 mobile sites within the Ericsson network-managed circle. Ethio telecom stated that the initiative will significantly improve network coverage, capacity, and quality through the replacement of legacy infrastructure with advanced technology.

https://www.fanamc.com/english/ethio-telecom-and-ericsson-sign-network-expansion-and-modernization-